የሐረሪ ህዝብ ክልላዊ መንግስት

# ሐረር ነጋሪ ጋዜጣ

# HARAR NEGARI GAZETA

OF THE HARARI PEOPLE REGIONAL STATE

| | | |
|---|---|---|
| 14 ኛ ዓመት ቁጥር 6<br>14 th Year No. 6 | | ሐረር መስከረም 21 ቀን 2002 ዓ/ም<br>HARAR, Oct , 1/ 2009 |
| ያንዱ ዋጋ ብር 4:00<br>Unit Price Birr 4:00 | በሐረሪ ህዝብ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ | የፓ.ሣ.ቁ. 272<br>P.O.Box 272 |


ማውጫ

ደንብ ቁጥር 33/2002

የሐረሪ ህዝብ ክልላዊ መንግስት የሐረር ቴክኒክና ሙያ ኮሌጅ ለአሰልጣኝ መምህራን የአካዳሚክ ማእረግ ለመስጠት የወጣ ደንብ ማሻሻያ ደንብ 500


## ደንብ ቁጥር 33/2002

## የሐረሪ ህዝብ ክልላዊ መንግስት የሐረር ቴክኒክና ሙያ ኮሌጅ ለአሰልጣኝ መምህራን የአካዳሚክ ማእረግ ለመስጠት የወጣ ደንብ ማሻሻያ ደንብ

የሐረሪ ህዝብ ክልላዊ መንግስት የሐረር ቴክኒክና ሙያ ኮሌጅ ለአሰልጣኝ መምህራን የአካዳሚክ ማእረግ ለመስጠት የወጣ ደንብ ከመውጣቱ በፊት በኮሌጅ ውስጥ በማሰልጠን ልምድ ያካበቱና በተከታታይ ስልጠናዎችን የወሰዱ አሰልጣኝ መምህራንን የአካዳሚክ ማዕረግ ተጠቃሚ ማድረግ አስፈላጊ በመሆኑ፤

የሐረሪ ህዝብ ክልላዊ መንግሥት የመስተዳደር ምክር ቤት በአዋጅ ቁጥር 70/99 በአንቀጽ 32/2 በተሰጠ ስልጣን መሰረት ይህንን ደንብ አውጥቷል፡፡

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ "የሐረሪ ህዝብ ክልላዊ መንግስት የሐረር ቴክኒክና ሙያ ኮሌጅ ለአሰልጣኝ መምህራን የአካዳሚክ ማእረግ ለመስጠት የወጣ ደንብ ቁጥር 25/2001 ማሻሻያ ደንብ ቁጥር 33/2002" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### 2. ማሻሻያ

የሐረሪ ህዝብ ክልላዊ መንግስት የሐረር ቴክኒክና ሙያ ኮሌጅ ለአሰልጣኝ መምህራን የአካዳሚክ ማእረግ ለመስጠት የወጣ ደንብ ቁጥር 25/2001 እንደሚከተለው ተሻሽሏል፡፡

1. በደንቡ አንቀጽ 13 የነበረው ንዑስ አንቀጽ 1 ሆኖ ንዑስ አንቀጽ 2 ተጨምሯል፤

" ደንቡ ከመውጣቱ በፊት በኮሌጁ በማሰልጠን ልምድ ያካበቱና በተከታታይ ስልጠናዎችን የወሰዱ አሰልጣኝ መምህራን በሰለጠኑበት ሙያ ወይም አብይ የትምህርት አይነት አማካይ ውጤት 2.5 እና በላይ ውጤት ባይኖራቸውም የአካዳሚክ ማዕረጉ ተጠቃሚ ይሆናሉ፡፡''

### 3. ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ ደንብ ከመስከረም 21/2002ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

ሐረር መስከረም 21/2002 ዓ.ም

ሙራድ አብዱልሀዲ

የሐረሪ ሕዝብ ክልላዊ መንግስት

ፕሬዝዳንት